## ማድረግ የምትችሉት

1. **ምልክቶቹን ተማሩ።** የኪስ ቦርሳ ውስጥ የሚገቡትን በ17 ቋንቋዎች ቁልፍ ምልክቶችን የሚገልጹትን መጠቆሚያ ካርዶቻችንን እዘዙ። እነዚህን ካርዶች በአካባቢያችሁ ያሉ ተጠቂዎችን ማግኘት የሚችሉ ሰዎች መካከል መበተን ትችላላችሁ። በይበልጥ ለመረዳት፡- *www.dhs.gov/Bluecampaign*

2. **የሰው ዝውውር ምልክቶች ስታዩ ጠቁሙ።**

   የሰው ዝውውር እንቅስቃሴ ስታዩ ለመጠቆም ወይም ከፌዴራል ሕግ አስከባሪ እርዳታ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 1-866-347-2423 ደውሉ ወይም በኢንተርኔት ላይ በ www.ice.gov/tips አድራሻ በኩል ጥቆማ አቅርቡ።

   በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ወንጀል በሚጠረጥሩበት ጊዜ የአገር ውስጥ ደህንነት ምርመራዎች (Homeland Security Investigations' (HSI)) መጠቆሚያ የስልክ መስመር ጋር በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን በዓመት ሁልቀን መደወል ይችላሉ። የመጠቆሚያ መስመሩ ጋር በዓለም ላይ ከየትም አገር በስልክ ቁጥር 802-872-6199 መደወል ይቻላል። ከፍተኛ ስልጠና ያላቸው ባለሙያዎች ከሕዝብም ሆነ ከሕግ አስከባሪ ድርጅቶች ከ400 በላይ HSI ከሚያስከብራቸው ሕጎች ጋር የተያያዙ ጥቆማዎችን፣ ከሰው ዝውውር ጋር የተያያዙ ጥቆማዎችን ጨምሮ ይቀበላሉ።

   **ብሔራዊ የሕገወጥ ሰው ዝውውር መረጃ ማዕከል (National Human Trafficking Resource Center (NHTRC)) ጋር በስልክ ቁጥር 1-888-373-7888 በመደወል የሚከተለውን ማድረግ ትችላላችሁ፡-**

   - እርዳታ ማግኘትና አካባቢያችሁ የሚገኝ አገልግሎት ሰጪ ጋር መገናኘት፤
   - ሕገወጥ የሰው ዝውውር ሲካሄድ መረጃ መስጠት፤ ወይም
   - ስልጠና፣ ቴክኒካዊ እርዳታ ወይም ሌላ ነገር በመጠየቅ በይበልጥ መረዳት።

   NHTRC ከየትም ከአገር ውስጥ የሚመጡ ጥሪዎችን በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን፣ በዓመት በእያንዳንዱ ቀን የሚቀበል ብሔራዊ

   የነጻ ስልክ መስመር ሲሆን የሚተዳደረውም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ነው።

3. **እራሳችሁንና ማህበረሰባችሁን አስተምሩ።** ስለ ሰው ዝውውርና ሌሎች ማወቅ ስለሚገባችሁ ምልክቶች በይበልጥ ለማወቅ በኮምፒዩተር የምንሰጠው አሳታፊ ነጻ ሥልጠና ውሰዱ፣ ሌሎችንም የምታውቋቸውን ሰዎች እንዲወስዱ ጠይቁ። ይህንን ጎብኙ፡- www.dhs.gov/bluecampaign።

4. **መለዕክቱን አስተላልፉ!** ስለ Blue Campaign እና ስለምናቀርባቸው የተለያዩ ፕሮግራሞች ለሥራ ባልደረቦቻችሁ፣ ለቤተሰብና

   ለማንኛውም ፍላጎት ላለው ሰው ንገሩ። ለማግኘት፡- www.dhs.gov/bluecampaign።

5. **የ Blue Campaign ድህረ ገጽን ጎብኙ።** ተጨማሪ ሥልጠና፣ የመረጃ ማካፈያ መጽሔቶች፣ የተጠቂ እርዳታ መጽሔቶች እና ሕገወጥ የሰው ዝውውርን ለማቆም በሚደረገው ትግል ለመሳተፍ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ ገጽ ጎብኙ፡- www.dhs.gov/Bluecampaign። ፌስቡክ ላይ በሚከተለው ገጽ "Like" አድርጉን፡- www.facebook.com/bluecampaign። ወይም በሚከተለው ኢሜል ጻፉልን BlueCampaign@hq.dhs.gov።



የተጠቂ መለያ
NGO,
በኃይማኖት የተመሠረተ ቡድን

# *ምን ማድረግ ትችላላችሁ?*

*በሕገወጥ የሰው ዝውውር የተጠቁ ሰዎችን መለየት መቻልና መጠቆም*

# ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

### *በሕገወጥ የሰው ዝውውር የተጠቁ ሰዎችን መለየት መቻልና መጠቆም*

## ተጠቂዎች ፊትለፊት ናቸው

አስተማሪዎች፣ ነርሶች፣ ማህበራዊ ሠራተኞች፣ በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ መሪዎች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO) የማህበረሰቡ አባል ሲሆኑ የሰው ዝውውር ተጠቂዎች የማግኘትና የማለየት እንዲሁም የመርዳት እድላቸው ከፍ ያለ ነው። የሰው ዝውውር ምልክቶችን ማወቅ ይገባችኋል። ተጠቂዎችን ለይቶ አውቆ ሰው አዘዋዋሪዎችን ሕግ ፊት በማቅረብ የማህበረሰባችንን ደህንነት ለመጠበቅ ይህ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

## የሰው ዝውውር ተጠቂዎች በማህበረሰባችን ውስጥ አሉ

## የዝውውር ተጠቂዎች ማንኛውም ዕድሜ፣ ዘር፣ ጾታ ወይም ዜግነት፣ የአሜሪካ ዜጎችን ጨምሮ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአገር ውስጥ የኑሮ ሁኔታቸው ሕጋዊ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ተጠቂዎች ሕጋዊም ሕገወጥም የሥራ ረድፍ ውስጥ ተሰማርተው ይገኛሉ፤ አንዳንዶቹ በውሸት ጥሩ ክፍያ ያለው ሥራ ታገኛላችሁ ተብለው ወይም በፍቅር ተታልለው ይገባሉ። የአምልኮ ቦታ ውስጥ፣ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ቤቶች ውስጥ፣ ሆቴሎች ውስጥ፣ ሬስቶራንቶች ውስጥ፣ የግንባታ ቦታዎች ላይ፣ እርሻዎች ላይ፣ የአውቶቡስና የባቡር ጣቢያ ውስጥ፣ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ፣ የአካባቢ መናፈሻ ቦታ ላይ፣ የጭነት መኪና ፌርማታ ላይና የሃይዌይ ማረፊያ ቦታ ላይ ወይም የማሳጅ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶችና ስትሪፕ ክለቦች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ በቤት ውስጥ አገልግሎት፣ በእርሻ ወይም ፋብሪካ ሥራ ወይም ሌሎች ዓይነቶች የግዴታ ሥራ ወይም ጋለሞተኝነት ላይ ይሰማራሉ። በፌዴራል ሕግ መሠረት ከሕጋዊ ዕድሜ በታች ያሉ ጋለሞታ ሆነው የሚገኙ ወጣቶች የሰው ዝውውር ተጠቂዎች ናቸው።

## ሰው አዘዋዋሪዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ

ሰው አዘዋዋሪዎች የሚያደቡት ብዙም ማህበራዊ ድጋፍ የሌላቸው ሰዎች ላይ ነው። የገንዘብ ችግር ያለባቸው፣ ቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስባቸው፣ የተፈጥሮ ቀውስ ወይም የፖለቲካ አለመረጋጋት ተጠቂዎች ወይም በተለያየ ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ይፈልጋሉ። አዘዋዋሪዎች ተጠቂዎችን ለማጥመድና ተገዢ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ፣ ማጥቃትን ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ተጽዕኖን ጨምሮ። ስነልቦናዊ ጠባሳው ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ ብዙዎቹ እራሳቸውን እንደ ተጠቂ ላያዩ ወይም እርዳታ ላይጠይቁ ይችላሉ፣ በግላጭ ሕዝብ ያለበት ቦታ ላይ ቢሆኑም።

የሰው አዘዋዋሪዎች ብዙ ጊዜ የሚንቀሳቀሱበት መንገድ:-

- ግለሰቡን ወይም የግለሰቡን ቤተሰብ በማጥቃት ወይም በማስፈራራት፤
- ግለሰቡን በመጉዳት ወይም መደበኛ ነገሮች በማሳጣት፣ ለምሳሌ ምግብ፣ ውሃ ወይም እንቅልፍ፣
- በውሸት ፍቅር ወይም ጓደኝነት በማታለል፣
- ጥሩ ሥራና ቤት እንደሚገኝ በውሸት ቃል በመግባት፣
- ተጠቂው አምልኮ ቦታ መሄድ እንዳይችል በማገድ፣
- ከጓደኞችና ቤተሰብ ጋር እንደልብ እንዳይገናኝ በማድረግ፣
- የመንቀሳቀስ ነጻነት በማሳጣት፣
- የግለሰቡን መታወቂያና ሰነዶች በመቆጣጠር፣
- ከአገር ትባረራለህ/ሽ ወይም ፖሊስ እጠራብሃለሁ/እጠራብሻለሁ ብሎ በማስፈራራት፣ እና/ወይም
- እዳ አለብህ/ሽ በማለት እዳውን ለማስከፈል ከደሞዙ/ዟ ማስቀረጥ

## የሕገወጥ ሰው ዝውውር ምልክቶች

ተጠቂዎችን ለይቻችሁ አዎቃችሁ ጥቆማ በምታደርጉበት ወቅት፣ ሕግ አስከባሪዎች ተጠቂዎችን ማዳን እንዲችሉ ድርሻችሁን እያደረጋችሁ ነው፣ ሕይወትም ታተርፉ ይሆናል። ተጠቂዎች ነጻነታቸውንና ክብራቸውን መልሰው እንዲያገኙ የሕክምናና የአእምሮ ጤንነት ምርመራ፣ መጠለያ፣ የሥራ ሥልጠናና የሕጋዊ እርዳታ አገልግሎት እንዲያገኙ መርዳት ትችላላችሁ። የእናንተም ሆነ የተጠቂው ደህንነት መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው። መቼም ቢሆን የተጠረጠረን አዘዋዋሪ አትጋፈጡ፣ ተጠቂንም ጥርጣሬያችሁን በተመለከተ አታሳውቁ። የአንድ ምልክት መኖር ወይም አለመኖር የሰው ዝውውር ለመኖሩ መረጃ ላይሆን ይችላል። የሰው ዝውውር አለ ተብሎ ጥርጣሬ ሲኖር ምርመራ የማድረግ ፋንታ የሕግ አስከባሪዎች ነው።

- ግለሰቡ ከቤተሰቡ፣ ከጓደኞች፣ ከማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም ከአምልኮ ቦታዎች የተገለለ ይመስላል?
- ልጁ/ልጅቷ ትምህርት ቤት መሄድ አቁሟል/አቁማለች?
- ግለሰቡ ድንገተኛ የባህርይ ለውጥ አሳይቷል?
- ወጣቱ/ቷ ልጅ የጋለሞታ ድርጊት ውስጥ ገብቷል/ገብታለች?
- ግለሰቡ ያለበትን የማያውቅ ወይም ግራ የገባው ወይም የአእምሮና የሰውነት ጉዳት የደረሰበት ይመስላል?
- ግለሰቡ በተለያየ የመዳን ደረጃ ላይ ያሉ ቁስሎች ይታዩበታል?
- ግለሰቡ የፈራ፣ ዝምተኛ ወይም ተገዢ ይመስላል?
- ግለሰቡ ምግብ፣ ውሃ፣ እንቅልፍ ወይም ሕክምና የተነፈገ ይመስላል?
- ብዙውን ጊዜ የሚናገርለት ሰው ከግለሰቡ ጋር አብሮ አለ? ወይም ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር የሚመስል ሰው፣ ለምሳሌ ማንን እንደሚያናግር ወይም የት እንደሚሄድ የሚቆጣጣር ሰው ያለ ይመስላል?
- ግለሰቡ እንዴት መልስ እንዴት መስጠት እንዳለበት የተነገረው ይመስላል?
- ግለሰቡ ለመኖር በማያመች ሁኔታ እየኖረ ነው?
- ግለሰቡ የግል ንብረት የለውም ወይም የተረጋጋ የመኖሪያ ሁኔታ የለውም?
- ግለሰቡ የእንቅስቃሴ ነጻነት አለው? ግለሰቡ በፈለገው ጊዜ ተነስቶ ከሚኖርበት ቦታ መሄድ ይችላል? አግባብ የሌላቸው የጥበቃ ሁኔታዎች አሉ?

BLUE CAMPAIGN
One Voice. One Mission. End Human Trafficking.™